# አሰፋ ጫቦንስ ከፍተን ብናያቸው?
# ጌታቸው ረዳ (ኢትዮያጵያን ሰማይ አዘጋጅ)



Above Photo Asefa Chabo published@Ethiopian Semay blog

እንደምን ሰነበታችሁ? ይህ ጽሑፍ “ለአቶ አሰፋ ጫቦ የጻፍኩት ደብዳቤ ያልተምለሱ ጥያቄዎች” ከሚለው ክፍል አንድ የቀጠለ ክፍል ሁለት ነው። ለበርካታ አመታት እንደገለጽኩት (ብርሃኑ ነጋ እና በርቱካን መዲቅሳ ቅንጅትን አፍርሰው ወደ እዚሁ አሜሪካ ሲመጡ ጀምሮ ) ወደ ወያኔ እንዳናተኩር እንቅፋቶች የሆኑን “ወየኔን ሲያገለግሉ የነበሩ ወይንም ከወያኔ ጋር የተቃቡ፤የተሻሹ “ትንሽ አፈር ከማይሉ” ጋር እንደሆነ እና ትግላችንም ያውም ካንዳንዶቹ ምናልባትም በጦርነት እንደሚሆን ስጸፍ ብዙዎቹ አላመኑኝም።ማመን ብቻ ሳይሆን “ተቃዋሚን እንዴት ትቃወማለህ” የሚሉ “ጪሂዎች” የስድብ ናዳ አውርደውብኝም ነበር። ሆኖም ልክ ነበርኩ።ዛሬ ትኩረታችን ወደ እነሱ የሆነበትም መነሻ ፤ ከወያኔ ጋር ሲተሻሹ የተለከፉበት አገርሺ በሽታቸው እያገረሸባቸው እየተላከፉ አስቸግረዋል። ከነዚህ አንዱ አቶ አሰፋ ጫቦ ሆነው ማየቴ እጅግ አዝኛለሁ።

ነገሩ በሞረሽ ወገኔ ሊቀመንበር አቶ ተክሌ የሻው እና በእሳቸው መሪነት የተጻፈው በአማራ ሕብረተሰብ ላይ ስለደረሰው ግፍ የሚያጋልጥ “ምጽአተ አማራ…” የሚባል መጽሐፍ ስለተጻፈው ጉዳይ አንስተው “አስቀያሚ ትችትና ስድብ” በየመድረኩ ጽፈው በመበተናቸው መሆኑን ከተቸሁት ክፍል 1 ጽሑፌ ታስታውሳላችሁ። ለነገሩ እኚህ ሰው እንኳን ለአቶ ተክሌ የሻው ይቅርና “ልዩ አክብሮት ያለኝ ጥብቅ ወዳጄ” እያሉ <u>በአንቱታ</u> ሲጠሩዋቸው የነበሩትን መሪያቸውና ወዳጃቸው ሊቀመንበር መንግሥቱ ሃይለማርያምን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ምን አንዳደርጉዋቸው አላወቅኩም “እሱ/አንተ” እያሉ መዘርጠጣቸው ማስተዋል ጀምረዋል (የባንዳ ልጅ እና እሱም ባንዳ ሆኖ የዘለቀው የዳዊት ወ/ጊዮርጊስ <u>ሲንድሮም</u> የተጋባባቸው አይነት መሆኑ ነው መሰለኝ)። በዚህ የባሕሪ ለውጥ አስምልክቼ ስለገረመኝ “አቶ አሰፋ ምነው ሊቀመንበር መንግሥቱን በቲ/ቪ እና በጽሑፍዎ “በእሱታ/እሱ” እያሉ መጣራት ጀምሩ? ብየ በደብዳቤ ልኬ ይድረስ አይድረስ አላውቅም/መልስ አላገኘሁም።

አቶ አሰፋ ጫቦ ብርቱ ጸሓፊ ፤ ንግግር ፈጣሪና ማራኪ አንደበት ያላቸው ፖለቲከኛና የሕግ ምሁር ናቸው። ብርቱ ጸሐፊዎችና ተናጋሪዎች ሆነው የተፈጠሩ ሰዎች በአፍዝዝ አደንዝዝ (ሂፕነታይዝ) ገመዳቸው ጎትትው በመጥለፍ እንዳሻቸው አድርገውናል። ከማስታውሳቸው መሃል 'አብርሃ ፓትሪስ' (የትግራይ ሰው። ወያኔን "የመንደር አይጥ" የሚል ቅጽል ስም የሰጠ)፤ ሳሞራ የኑስ መቀሌ ከተማ በጭለማ ተሸሽጎ ከበረሃ አድብቶ በመግባት በሳሞራ የኑስ አልሞ ተኳሽነት የተገደለ ፤ ዋለልኝ መኮንን (አማራ፤ወሎየ) ፤ ብርሃኑ ነጋ (ጉራጌ) አሰፋ ጫቦ (ጋሞጎፋ) መንግሥቱ ሃይለማርያም፤ መለስ ዜናዊ፤ ሙሉጌታ ሉሌ (ጎጃሜ)፤ የሱፍ ያሲን (ዓፋር)፤ ወዳጄ እያሱ አለማዮህ/ሃማ ቱማ (ኢሕአፓ)፤ ልደቱ አያሌው.... ወዘተ...ወዘተ የሚጠቀሱ ብርቱ ጸሐፊዎችና ተናጋሪዎች ናቸው። ስለሆነም በተለያዩ መነሻዎች ብዙዎቻችን የነሱ ተገዢዎችና አድናቂዎች ሆነናል።

አቶ አሰፋ በብርቱ ብዕራቸው ብዙዎችን እኔኑንም ሳይቀር አነሁልለውናል (በተራቸው እሳቸውም ሓዋርያ በሚባል የካናዳ ጋዜጣ ስጽፍ በነበረበት ወቅት የየኔን ብዕር እንደሚማርካቸው ባንደበታቸው ገልጸውልኛል)። ስለሆነም እሳቸው በሚጽፏቸው ጽሑፎች ያልተማረከ አንባቢ አለ ለማለት ይቸግራል። በዚህ ተሰጥቶአቸው ብዙ ነገሮችን እያምታቱ ሃቁን እየደበቁ እንደተጓዙ አሁን አሁን መለስ ብየ የሚጽፉዋቸው እና ቀደም ብለው የደረግዋቸው/የተሳተፉባቸው/ የተናገርዋቸው ነገሮችን ሳገናዝብ ሰውየው ፍጹም ከሚጽፉዋቸው ጋር ጭራሽ የማይገጥሙ ራሳቸውን ነጻ የሚያወጡ ሆነው አይቻቸዋለሁ።

በቅርቡ አንድ ነገር ስፈትሽ እሳቸው የተሳተፉበት **"የሽግግር መንግስሥትና የሽግግር ምክር ቤት አባል ነበርኩ"** ባሉበት የወያኔ (የአገር ገዳዮችና የፋሺስቶች ምክር ቤት) ውስጥ የተናገሩት እና ዛሬ ስለ ኤርትራ ግንጠላ፤ታሪክ፤ ስለ ኢሳያስ አፈወርቅ/ስለ ወያኔ ቲያትር ሰሪነትና እቡይነት፤ስለ አነግ ወዘተ እያነሱ በማራኪ ብዕራቸው አንባቢን ሲያነሆልሉ ከርመዋል። ሌሎቹን "እገሌን....ከፍተን ብናይ" "መትፋት ያስነውራል" ወዘተ..... እያሉ ከፍተው አሳይተውናል። የስለላው ድርጅት "ሲ አይ ኤ" ሊቀጥረኝ ብዙ ጊዜ ሞክሮ "እመቢ" አልኩት ይላሉ። 'በአንድ ራስ ሁለት ምላስ' ዓይነቱ ሆኖው ሳገኛቸው ፤በጣም ገርሞኝ **"አሰፋ ጫቦንስ ከፍተን ብናያቸው"** በሚል ትንሽ ለማለት ወሰንኩኝ።

እዚህ ላይ በወንጀል የሚከሰሱበትን እዚህ አላነሳም። እዛ ውስጥ የራሴን ድምዳሜና ግንዛቤ ለመውሰድ ካልሆነ (ስለማላውቃቸው) በርግጠኛነት ሰርተዋል ብየ የምጠቁመው ነገር የኝም። ስለ ተናገሩትና ስለሚጽፉት ግን አንድ ለማለት ተገድጃለሁ። ከአቶ አሰፋ ጫቦ የታዘብኩት የሁሌ ንግግራቸው አንድ ነገር አለ። ከአናሳ ማሕበረሰብ መወለድ ልዩ ጠቀሜታ የሚያስገኝ እየመሰላቸው ይሁን አይሁን አላውቅም የተወለድኩት እጅግ አነስተኛ ከሚባሉት " ከተጨቆኑብሄረሰቦች" የተወልደኩ ነኝ እያሉ በምክር ቤቱም ሆነው ከዚያም እዚህም ሆነው ያንን እየደጋገሙ ልዩ ትኩረት ለማግኘት (አላውቅም) (?) ሲመጻደቁ በተደጋጋሚ አንብቤአቸዋለሁ/አድመጬአቸዋለሁ። ስለሆነም ከአናሳ ብሔረሰብና ከተጨቆኑት

ማሕበረሰቦች የመጣሁ ስለሆንኩ (ጨቋኙ ማን እንደነበር አይገልጹም) የሚሉት አመል አላቸው። ከአናሳ ብሔረሰብ የተገኘሁ ነኝ ስለሚሉም፤ ጭቁን በመሆናቸውም ዛሬ "ዕቡይ" እያሉ የሚዘልፉት ፋሺስትና ነብሰገዳይ ኢሳያስ አፈወርቂን "የዓለም ተምሳሌት፤ለእኛ ለደቡብ ጭቁን ሕዝቦች አርአያ ናችሁ፤ እንኳን ለነጻነታችሁ ችቦ አምቦገቦጋችሁ….." እያሉ ሲያወደሱ የሰማ ጆሮ እውነትም ምንኛ በብርቱ ጸሐፊዎችና ተነጋሪዎች እየተታለልን እንደሆንን 'አቶ አሰፋ ጫቦ' ዓይነተኛ ተምሳሌት ናቸው።

የቁርጥ ቀን ልጆች የሆኑት ጠመንጃ በግምበራቸው ተደቅኖባቸው፤ እነ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ፤ እነ ታማኝ በየነ በዛው በቀውጢ በዚያው የመከራና የፈታኝ አስፈሪ ሰዓት፤ የሻዕቢያና የወያኔ ነብሰ ገዳዮች የአዲስ አበባ ኗሪዎችን፤መንደሮችን፤ አስፋልቶችን፤ መውጪያ መግቢያ በሮችን በተቆጣጠሩበት በሚያስፈራው በዚያው በ1981 ዓ.ም ወቅት "ለነብሳቸው ሳይሳሱ" በቁጭትና በእልህ "አንድ ኢትዮጵያ" "አንድ ሰንደቃላማ" "ኢትዮጵያ ! ኢትዮጵያ" እያሉ በፏሲስቶች መሃል ሲያቅራሩ፤ሲፎክሩ፤ ሲዘምሩ፤ ሲሟገቱ፤ እነ አቶ አሰፋ ጫቦ "ኦሞቲክ" የሚል የብሔሮች (?) ድርጅት መስርተው <u>የወያኔ ሰርገኛ</u> ሆነው የሽግግርና የምክር ቤት አባል ሆነው በነበሩበት ወቅት የተናገሩትን እናስታውሰለን።

አስሬ የሚዋሹን አባባል አላቸው "<u>በድምፅም በምስልም የተቀረጸ ስለሆነ የታሪክ ተመራማሪዎች ሊያገኙት ይችላሉ….</u>" በማለት ያላሉትን አልኩኝ እያሉ የሚመጻደቁበት አባባል አላቸው። በዚያ ሳይወሰኑ እራሳቸውን ነፃ አውጥተው ሌሎችን **"የወያኔና ሻንጣ ተሸካሚዎች"** የሚሉት "ንጽሕና" አላቸው ። እንዲህ ይላሉ፤

"**ኢሳይያስ አፈወርቂን በአካል ያየሁት ነሐሴ 1981 አፍሪቃ አዳራሽ ወያኔና ሻንጣ ተሸካሚዎቹ አዲስ አበባ ገብተው ባዘጋጁት "የሰለምና ዲሞክራሲ ጉባዔ" ላይ አፍሪቃ አዳራሽ ነበር።**" ይላሉ። እሳቸው ምን ተሸክመው እንደገቡ እንመልከት።

ስለ ኤርትራ ጉዳይ አገር ወዳዱ እና አርበኛው የተከበሩ የቀዶ ጥገና ሓኪም ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ 'የኤርትራን ነፃነት በሚመለከት" ሲናገሩ ይህ ቤት ስለ ኤርትራ እና ኢትዮጵያ አንስቶ ውሳኔ ለማሳለፍ መብት/ማንዴት/ የለውም። በታሪክም የሚደገፍ አይደለም" ሲሉ በግልጽ ሲቃወሙ ዛሬ በብዕራቸው የሚመጻደቁብን አቶ አሰፋ ጫቦስ 'ፕሮፌሰር አስራትን ተቃውመው፤ <u>ኢሳየስ አፈወርቅ እና "አፈ ክፍቱ" ሟቹ የሲዳማው ወልዳማኑኤል ዱባለን</u> (በጣም አስኮናኝ የነበረ ግለሰብ ከኤርትራ በላይ ኤርትራ ሆኖ ሲቀደድ የነበረ) በመደግፍ አቶ አሰፋ ጫቦ ምን ሲሉ ነበር?

እንዲህ ሆነ (በቪዲዮው ላይ የተቀረጸ ማስረጃ)፡-

አቶ አሰፋ እጃቸው አወጡ፡

***መለስ ዜናዊ፤-***

እሺ አቶ አሰፋ (ይላቸዋል የጉባው ሊመቀነበር መለስ ዜናዊ)

***አቶ አሰፋ ጫቦ፤***

ስለ ኤርትራ ጉዳይ በፕሪንሲፕሉ በሚባለው ነገር አብዛኛው ተደጋግሞ በተለያየ መንገድ (ይሁን) እንጂ ተብሏል። ጥዋት ከተደረጉት ንግግሮች አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ እና አቶ ወልደ አማኑኤል የተናገሩት አለ፡ "ያኛው የታሪክ ነገር" የተነሳው "አካዳሚክ" ጥያቄ ነው" ይሄ የፖለቲክ ጥያቄ ነውና ከሱ ጋራ አይሄድም ከሱ ጋራ ወደፊት ለመጠናት በቂ ጊዜ አለ የተባለው በእውነትም ተገቢ ነው። ታሪክ እያነሳን ጊዜ የምናጠፋ እይመስለኝም።…"

ይላሉ አቶ አሰፋ ጫቦ ዛሬ "ዕቡይ" እያሉ ለሚዘልፉት ኢሳያስ አፈወርቂን ድጋፍ በመስጠት፤ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስን በመቃወም።

ታስታውሱ እንደሆነ ፕሮፌሰር አስራት የኤርትራ ጉዳይ ለመወሰን እዚህ ከመጣን በታሪክም በሕግም የሚያስኬድ አይደለም፡ ብለው ታሪክ እና ሕጋዊነትን እያጣቀሱ በተመተንተን (ያውም በመለስ ዜናዊ ንግግራቸው እንዲቋረጥ እየተደረገ) ይህ ጉባኤ የመወሰን ማንዴት/መብት የለውም ስላሉት የመከራከሪያ ሃሳብ፤ በመቃወም "ጋጠ ወጡ" ኢሳያስ አፈወርቅ "ይህ ለትምህርት ቤቶች የሚተው የአካዳሚ ጥያቄ" ነው ብሎ የፕሮፌሰሩን ሕጋዊ ትንተና ባጣጣለበት አንደበት ነው አቶ አሰፋ ጫቦ "ኢሳያስን ደግፈው" ኢትዮጵያዊው ፕሮፌሰር አስራትን በሕዝባችን ፊት እና በባዕዳን ታዛቢዎች፤ጋዜጠኞች ጀሮና ዓይን ፊት ለማንኳሰስ የተናገሩት ንግግር ነው።

አቶ አሰፋ ጫቦ "ፕሮፌሰር አስራትን" ጊዜ እያባከኑብን ብቻ ሳይሆን፤ "ነጋሪት ጋዜጣ እስኪወጣ ብለን አንጠብቅም፤ ኤርትራን በቻርተሩ መሰረት ነፃነቷን አሁኑኑ ማግኘት መብቷ ነው፤አጽድቀነዋል…' ከማለት አልፈው በፏስቱ ኢሳያስ የተመራውን በጸረ ኢትዮጵያና በጸረ አማራነት 'ትግል' የተጎነጎነው የኤርትራ ትግል እንዲህ ሲሉ በአርአያነት ሲያሞግሱና ሲያሞካሹ እናድምጥ፡

እንዲህ ይላሉ አቶ አሰፋ ጫቦ ንግግራቸው በመቀጥል፤-

"(የኤርትራ ታጋዮችና መሪዎች) ለአፍሪቃና ብዙዎቹ ለተጨቆኑ ለዓለም ሕዝቦች በተለይ ወደ እኛው ወደ ደቡቡ/ሕዝቦች/ (ወደ እዛው እንደማንደርስ ተስፋ አደርጋለሁ) ትግሉ ምንም ያህል ጊዜ ቢወስድ "ነፃነት" ሊገኝ እንደሚችል ምሳሌ ናችሁ። በዓለም የነፃነት ትግል ታሪክ ውስጥ ምሳሌ የሚሆን ችቦ ያበራችሁ በመሆናችሁ፤ እንኳን ለትግላችሁ፤ እንኳን ለድሉ ለችቦው (ብርሃን) ማንቦግቦጉ አበቃችሁ ለማለት እፈልጋለሁ!"

ይላሉ አሰፋ ጫቦ ነሐሴ 1981 አፍሪቃ አዳራሽ ወያኔና ሻንጣ ተሸካሚዎቹ ጋር ሆነው "የሰለምና ዲሞክራሲ ጉባዔ" ላይ አፍሪቃ አዳራሽ ከተናገሩት የተወሰደ።

አቶ አሰፈ ጫቦ ኤርትራንን "ሲጨቁናችሁ የነበረው አማራን ድል መታችሁት" ብለው አስመራ ሄደው በትግርኛው "ዮሃና" (እንኳን ደስ አላችሁ) ማለት ነው የቀራቸው እንጂ "አማራን ድል መታነው" እያለ የሚቃዠው ኢሳያስ አፈወርቂን "በዓለም የነፃነት ትግል ታሪክ ውስጥ ተምሳሌት" ነህ ብለው አማራን የጨፈጨፈ ግፈኛ ሽፍታን ሲያሞጉሱ እንዳልነበር ዛሬ "ሽፍታ"፤"ዕቡይ" እያሉ የዋህ አንባቢዎችን በአኖህላሊ ብዕራቸው ሲያጃጅሉ ከርመዋል።ታሪክ ግን ለጊዜው ሊደብቁት ቢችሉ እንጂ እራሱ ከተቀበረበት ቆፍሮ የማውጣት ሃይል እንዳለው ብዙ ማስረጃዎች አይተናል።

አቶ አሰፋ ጫቦ ኢሳያስን ደግፈው፤ፕሮፌሰር አስራትን በመቃወም "አካዳሚክዎን" ለትምህርት ቤቶች መወያያ እንጂ በዚህ መድርክ ጊዜ አያባክኑብን ሲሉ ብቸኛውን ኢትዮጵያዊውን ሲሳለቁባቸው ማድመጥ እጅግ ይዘገንናል። ፕሮፈሰሩ የተከራከሩት ሕጋዊና ታሪካዊ ንግግር መሰረት ይዘው ነው።

አቶ አሰፋ እራሳቸው ያሉት አነጋገር እናስታውሳለን (በዚያው መድረክ) ፤ "በትግላቸው ከጨቋኞቹ/ ከዘረኞቹ/ከተረጨው መረዝ ...ነጥቀው ነጻነታቸው አግኝተዋል..." የሚሉት ዓይነት አባባል ባጭሩ በእንዲህ ገልጸውታል የኤርትራ 'ዲፋክቶ' መንግሥት "በትግሉ ነጥቆ ያገኘው ነው"። እንዲህ ከሆነ የኢትዮጵያን ሉዓላዊ የባሕር ወደብም ሆነ ሕዝብና መሬት "በሕግ ፤በታሪክ ሳይሆን፤ በትግሉ የነጠቀ ወረበላ/ሽፍታ/ወንበዴ" "በሕግም በታሪክም አልተደገፈም እና ይህ ጉባኤ የታሪክና የሕግ /ማንዴት /ሙብት/ የለውም" ነው የፕሮፌሰሩ ሙግት':: አቶ አሰፋ ኢሳያስን 'ደግፈው' ኢትዮጵያዊውን አርበኛ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስን (ሲናገር ለከት ያልነበረው ዛሬ በሕይወት የሌለ ጸረ አማራው 'አፈ ክፍቱ' ከሲዳማው ወኪል ከወልዳማኑኤል ዱባለ ጋር ሆነው) ለማንኳሰስ፤ ለማጣጣል "ጊዜ አያባክኑብን" ሲሉ ለማጣጣል የተሳተፉበት ጥቁር ነጥብ ታሪክ አልረሳውም።

አቶ አሰፋ በዚህ አላበቁም። አቶ አሰፋ 'ዕቡይ' (አሮጋንት/ባለጌ) እያሉ ዛሬ የሚዘልፉት የያኔው የአቶ አሰፋ ጫቦ "ተምሳሌታቸው" ኢሳያስ አፈወርቂ ድርጅት "ኢትዮጵያን የሚዘርፍበት ሁኔታ ሳያውቁ ያመቻቹለት መንገድ ያለ ይመስለኛል (እሳቸው ሁሌም ይመስለኛል ስለሚሉ የሳቸው ልዋሰና 'ያመቻቹለት ይመስለኛል"። እንዲህ ይላሉ፤-

"እዚህ ዶክሜንት ላይ የተገለጸው 'ኢ ፒ ኤል ኤፍ' ወይንም የኤርትራ ጊዜያዊ መንግሥት አዲስ አበባ ላይ 'ቢሮ' ይከፍታል ይላል። ባዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን ቢሮው በየቦታው ቢከፍትና ላለፈው ብዙ አመታት በጭፍን ዘረኝነት የተሞላበት፤ ጭፉኖች ያደረጉትን

ፕሮፓጋንዳ፤ ለመቀነስ፤ለማርገብ ከዚያም አልፎ ለማስተማር ዕደል ይፈጥርላቸዋል።.........” ይላሉ አቶ አሰፋ፡

‘ኢ ፒ ኤል ኤፍ’ ቢሮው በየቦታው መክፍት አለበት ሲሉ የሰጡትበት አስተያት ስንመለከት የሰነዘሩት ጉዳይ አለ። “ቢሮው በየቦታው ቢከፍትና ላለፈው ብዙ አመታት በጭፍን ዘረኝነት የተሞላበት፤ ጭፉኖች ያደረጉትን ፕሮፓጋንዳ፤ ለመቀነስ፤ለማርገብ ሲሉ “ማንን ነው በጭፍን ዘረኛነት እየከሰሱት የነበረው?” “ጭፍኖች ያደረጉት ፕሮፓጋንዳ” ሲሉ አማራውን ይሆን? ሌላ ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም ለኤርትራ ትግል መነሻ ተብሎ የሚነገረውና የሚከሰሰው “አማራ” የሚባለው ክፍል ነው። አይደለም እንዴ?

ስለሆነነም ኤርትራኖች ካንደበታቸው ከመሪ እስከ ደቂቅ “ኢትዮጵያ” የቅኝ ግዛት ይዛናለች አይሉም። እነሱ የሚሉት “አምሓራይ እዩ ገዚኡና” /የገዛን አማራ ነው/። የባሕር ወደብ ሲነሳም “የአማራዎች የነፍጠኖች ጥያቄ ነው” ሲሉ ነው የሚሰሙት። አይደለም እንዴ? መሪያቸውም (ኢሳያስ) “ሌሎች ቋንቋዎች አጣርቶ ሲናገር” አማርኛ እንዳይናገር ኢሳያስና እና ሌንጮ ለታ (ኢሳትና ፋሲል የኔአለምን ይጠቅሰዋል) በእንግሊዝኛ ሲናገሩ ወደ አማርኛ እየተተተረጎመ ነው ያደመጥነው። ስለዚህም አቶ አሰፋ ጫቦ በወቅቱ በጭፍን ዘረኝነት ውንጀላ እየከሰሱዋቸው የነበሩ ክፍሎች እነማን ይሆኑ? የመጀመሪያው ተከሳሽ አማራ ነበርና (የወቅቱ ታረጌት/ኢላማም አማራ ነበርና) ሌላ ተከሳሽ አልነበረም። አቶ አሰፋ ማንን እያሙ እንደነበሩ አልነገሩንም። ኢትዮጵያዊያን በኤርትራ ያደረግነው ጭፍን የጥላቻና የዘረኛነት ፕሮፓጋንዳ ያደረግነው አልነበርም እና አቶ አሰፋ ሊነግሩን ይገባ ነበር።

ብቻ እሳቸው (አቶ አሰፋ ጫቦ) ጉባው ላይ በጠየቁት መሰረት ሻዕቢያዎች በየክፍላተሃገራቱና ወረዳዎች ቢሮ/ ጽ/ቤት ከፍተው እህል፤ባሕርዛፍ፤ቡና፤በርበሬ፤ጥራጥሬ በገፍ ሌት ተቀን እያገዙ፤ ጥቁር ገበያ አስፋፍተው ኤርትራን ታይዋን ለማድረግ እቅዳቸው ተሳክቶላቸው 10 አመት (7 አመት) ኢትዮጵያን ለማራቆት መንገድ ተከፈተላቸው። ያ ብቻ ሳይሆን የተገላቢጦሽ ኢትዮጵያዊያን በገዛ አገራቸው ባይተዋር ሆነው “ደብረብርሃን ውስጠጥ” ኤርትራዊ አንድ ኢትዮጵያ በመኪና ገጭቶ “ፖሊስ ሲያስቆመው” እኔ ማን መስሎሃል?! “ኤርትራዊ እኮነኝ!!” ዞር በል! እኔን የማሰር መብት የለህም!" ብሎ ምራቁን አንደተፋበት እና ሳይጠየቅ እንደሄደ በወቅቱ በጋዜጦች ተዘግቦ እንደነበር ትዝ የለኛል።

ያ ብቻ ሳይሆን ትግራይም ጭምር እነ አቶ በድሩ አደምን (መ ኢ አድ አባል የነበሩ) በታክስ እና ቀረጥ (ግምሩክ) ሃለፊ ሆነው ሲሰሩ “ኤርትራኖች የሚያጋግዙት እህል እና ጥቁር ገበያ ለመቆጣጠር ሲሞክሩ “መቀሌ ውስጥ የነበረው የሻዕቢያ ኮንስላ ጽ/ቤት ሃላፊ” አርፈህ ተቀመጥ፤ካልሆነ ከእዚህ ንድትባረር አደርጋለሁ ብሎ ለአቶ በድሪ እንዳስጠነቀቃቸው ይተወሳል። ብዙ ብዙ ታሪኮች ማንሳት ይቻላል።

አቶ አሰፋ ጫቦ "የኢትዮጵያ ጭፍን ፕሮፓጋንዲስቶችና ዘረኞች" የሚሏቸውን ክፍሎች የፈጠሩት ዘረኛነትና ቁስል ለማርገብ ያመች ዘንድ (ኤርትራንን ከመባረር ለመከላከል ...ይሉታል ) "ሻዕቢያ አዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በየከተማው ቢሮ እንዲከፍት" ሃሳብ በሰጡበት መሰረት ሳይታወቃቸው "ቦይ" የመቦርቦርያ እና የትዕቢት" በር ከፍተውላቸዋል።

ብዙ ኤርትራ ተቃዋሚዎችም ወሎ እና ሌሎች ቦታዎች ሻዕቢያ ሰላዮችና ገዳዮችን በየቢሮው/በየከተማው አሰማርቶ ወንጀል ፈጽሟል (የራሱ ዕስር ቤትም መስርቶ ነበር)። ይህ ሁሉ ወንጀል እንዲፈጸም መንገድ ሲጠረግ ኢትዮጵያዊያኖች "የአካዳሚ ንትርካችሁን እያመጣችሁ ጊዜ አታቃጥሉብን"፤ ሲባሉ ኤርትራኖች ለደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች/ብሐሮች (?) ተምሳሌት አርአያችን ናችሁ እየተባለ በኢትዮጵያ ምድር ወረራ ሲፈጸም፤ ኢትዮጵያና ኢትጵያዊነት ወደ ቆሻሻ እንዲጣል፤ እንዲረገጥ፤ አማራው ሲወነጀል፤ሲገደል፤ለማኝ ሲሆን፤ሲባረር፤ መኮንኖች መለዮአቸውን መሬት ላይ አንጥፈው ሳንቲም እና ቁሯሽ እንጀራ ሲለምኑ ማየት፤ ጸያፍ ብሔራዊ ወንጀል ከሚፈጽሙትና ከፈጸሙ ጋር መደራረት፤መተሻሸት፤ ማሞካሸት ......ተጠያቀው ማን ነው? ምሁራን መልስ ስጡ እንጂ?!!!!!!!!!! ትምህርታችሁ ምንድ ነው? እንግሊዝኛ አጣርቶ መጻፍ?! ጠላት መወደስ? ንገሩን እንጂ! እስከመቸ እያሾፋችሁብን፤ እያጃጀላችሁብን እስከመቸ ድረስ ነው በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊ ማሕተም እየተሳለቃችሁ ያለምንም ተጠያቂነትን ውስጣዊ ሰቀቀን በነጻነት መኖር የምትችሉት! የተደረገው ወንጀል ስመለከት አምባ ይተናነቀኛል! ዛሬስ አልበቃችሁም!

ሰለ ንደቴ ይቅርታ አንባቢዎቼ። ልቀጥል፤

መጨረሻ አቶ አሰፋ ንግግራቸው በሚከተለው ሁኔታ ንግግራቸውን ደምድመዋል፡

"በተረፈ እንደገና እደግማለሁ ለአለም ሕዝብ ተምሳሌት በሚሆን መንገድ ነፃነታቸውን በጠመንጃ ነጥቀው ያገኙ ናቸው፤ ለሌሎቹ አርአያ ይሆናሉ፤ መልሰን የምንነጋገርበት አይደለም፤ ...."

ሲሉ የኢሳያስን ውምብድና፤ከሕደት፤ ማንነትን መካድ፤ ግድያ፤ዘረፋ፤ግርፍያ፤አማራ ወታደሮችን በባርነት ይዞ ናቅፋ በረሃና ሃሩር መንገድና ምሽግ ቆፋሪ አድርጎ "ማሰቃየትን" ጸረ አማራ፤ጸረ ኢትዮጵያ ትግልን በአርአያነትና በተምሳሌነት ያደነቁበትን ንግግራቸው ሻዕቢያን በማሞገስ ንግግራቸው *"አመሰግናለሁ ክቡር ሊቀመንበር"* ብለው ደምድመዋል።

ከአቶ አሰፋ ጫቦ፤ ከዳዊት ወልደጊዮርጊስ፤ ከካሳ ከበደ .... ወዘተ.... በታሪክ የመበላሸት ክስተት ኢትዮጵያዊያን ምሁራን ምን ትምህርት መቅሰም ትችላለችሁ? እነኚህ ምሁራን በማራኪ ብዕሮቻቸው እኛኑን ሲያዋልሉን፤ የተበተቡብንን ገመድ እንዴት በጥሰን ራሳችንን ነፃ ማውጣት እንችላለን ነው ጥያቄው? አቶ አሰፋ ጫቦ ከበረሃ አራዊቶች እና አማራን

ከጨፈጨፉ፤ካባረሩ የሰው ቋንቋ የሚናገሩ የሰው እንሳሳቶችና በጣም አስፈሪ ከሆኑ፤ እጃቸው በደም ከጨቀየ ወንጀለኞች ጎን እና ፊት ለፊት ተቀምጠው አርአያነታችሁን አደንቃለሁ እያሉ ሲያወዱስዋቸው ትንሽ ያልሰቀጠጣቸው "ምጽአተ አማራ.." መጽሐፍ ለማንበብ የፈሩበት ምክንያት እስካሁን ግልጽ አልሆነልንም። ይህንን ምስጢሩን ዘርዘር አድርገን በሚቀጥለው እንነጋገርበት ይሆናል። ትዝብቱ ለናንተው ትቻለሁ። አመሰግናለሁ፤ ጨርሻለሁ። ጌታቸው ረዳ ( Ethiopian Semay አዘጋጅ) getachre@aol.com